በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# በሠለጠነው ዓለምም ቢሆን ትክክለኛው ምርጫ በክርስትናችን ጸንተን መኖር ነው

መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
ኅዳር ፲ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# እንደ ክርስቲያን በሠለጠነው ዓለም የሚገጥሙን ፈተናዎች?

በ#ሃይማኖት; ስም የሚንቀሳቀሱ መበራከት

አክራሪነት

ያለ ቅድስና መኖር መስፋፋቱ

ምሳሌ፡- ሲጋራ ማጤስ፡ አልኮልና አደንዛዥ እጾችን መጠቀም፡ ግብረ ሰዶማዊነት

በቁሳዊ አስተሳሰብ መመራትና ዋጋ ወይም ትርጉም በሌላቸው ነገሮች መደሰት እያደገ መሄዱ(ያለ አግባብ የዋጋ ጭማሪ)

በርካታ ቤተሰብ በተለያየ ተራ ምክንያት መበተኑ

የፍቺ ቁጥር በየጊዜው እያደገ መሄዱ

ሃይማኖታዊ ኑሮ ጊዜ ያለፈበት አኗኗር ሆኖ እየተቆጠረ መምጣቱ

# በነዚህ ሂደቶች እርካታን አግኝተናል?

ሁላችንም ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባን ጥያቄ ነው፡፡

ከእግዚአብሔር ርቃ በምትኖር ዓለም ደስተኛ ነን?

እግዚአብሔር ደስ ያሰኘን ዘንድ በቂ ዕድል ሰጥተነዋል?

በፍላጎታችን ላይ መደራደር ወደ ቅድስና ለመድረስ ከያዝነው ግብ ይገድበናል?

ለዓላማችን ትኩረት በመስጠት ሁሉን እናስባለን?

ምንስ ማድረግ ይገባናል?

# ምን እናድርግ?

#ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ አይደለም።;

1ኛ ቆሮንቶስ 10 * 23

- አንዱን ሕግ ማክበር ይጠበቅብናል። ሕጉም የክርስቶስና የፍቅር ሕግ ነው።

- ይህም ወደምንታገዝበትና ወደ ምንማርበት ጎዳና ይመራናል።

- በቤተ ክርስቲያን ለምናገኛቸው ለወንድሞቻችንና ለእህቶቻችን ለውድቀታቸው ምክንያት መሆን የለብንም።

- #ሥጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው።; ሮሜ 14 * 21 እንደተባለ ራሳችንን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም መመልከትና መጠበቅ ይኖርብናል። በተጨማሪም...

# ዘወትር በቅድስና እንኑር

#የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።:;

1ኛ ቆሮ 3 * 16 - 17

# ወደ ብቃት/ታላቅነት እንዴት እናድጋለን?

ኃላፊነት የሚሰማን መሆን፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከቤተክርስቲያን፣ ከመምህራን፣ ከነፍስ አባቶቻችን በተማርነው መሠረት ተጠያቂነት ያለበት ውሳኔ በሕይወት ጉዞአችን ሁሉ በመወሰን፡፡

ጊዜያዊ ደስታ ወይም ጥቅም ላይ ተመስርተን የምንሠራውን ሁሉ መርምረን በመተው

ሁሉን በመቀበል በማመስገንና ይቅር በማለት

ሁሉን በሕይወታችን በሚያከናውነው በክርስቶስ አማካይነት የሕይወታችንን ዓላማን ፍልስፍና በመወሰን

እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ ሁልጊዜ እንዳለ በማስተዋል

የምንሠራውን ሁሉ በመመርመር፡ በመሥራት ላይ የምንገኘውን ሥራ ለምን እንሠራዋለን? እግዚአብሔርን እናከብርበታለን? መድኃኔዓለምን ልንገናኘው እንሻበታለን?

# ምንን እናስወግድ?

- የማንቆጣጠረውን ስሜት
- ያለ እግዚአብሔር ባለ ራዕይነትን
- በእግዚአብሔር ጸጋ ያልታገዘ ሥራችንን
- ምድራዊውን ከሰማያዊው በላይ ማድረግን
- ፍቅር አልባ መሆንን
- የክርስቶስ አካል ከሆነች ከቤተ ክርስቲያን መለየትን

# ፈቃደ እግዚአብሔር እንዴት ትገኛለች?

- ከቃሉ
- ከቤተ ክርስቲያን
- ከቅዱሳኑ
- በእግዚአብሔር ፈቃድ እየኖሩ ከሚመሩን ወዳጆቹ ምሪት
- በውጭ ልናየው ከምንችለው የእግዚአብሔር የእጁ ሥራ
- በእምነትና በጸሎት ከሆነ ሕይወት
- በርጋታ ከማሰብ፤ ከበቂ ምክንያት፤ ከትዕግሥት፤ ከተስፋ
- ራስ ወዳድነትና ምግባረ ብልሹነት የሠለጠነበትን አካሄድ በመቃወም ወይም በመጥላት

# መወያያ ነጥቦች

- ጸሎቴ ሁሉ ትርጉም አልባ የሆነ ስለሚመስለኝ የእግዚብሔር ፈቃድ ይሆንበታል ባልኩት ነገር መልሼ እረበሻለሁ። ምን ባደርግ ይሻላል?

- ልቅ ወሲብ፤ የዕፅ ሱሰኝነት፤ ጠጪነት፤ የክፉ ጓደኞች መልዕክት በሚተላለፍበት ፊልም የተጥለቀለቅን ስለሆንን ይኽን እንሸሽ ወይስ እንጋፈጠው? በሠለጠነው ዓለም ውስጥ ክርስቲያኖች ድርሻቸን ምንድር ነው?

- አሁን አርጅቻለሁ ብዙ ኃላፊነቶችም አሉብኝ። ይሁን እንጂ በቀረ ዘመኔ በእርግጥ ማድረግ ያለብኝ ምን እንደሆነ አላውቅም። ምን ባደርግ ይሻለኛል?

የሚቀጥለው ሳምንት ርዕሳችን፡-

# የቤተክርስቲያንን ትምህርቶች እንዴት እንስማ?

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

ይቆየን።